# የተስማሚ ቴክኖሎጂ አቅርቦት አመራረትና ስርጸት ዋና የስራ ሂደት የሚያከናውናቸው ዋና ዋና አገልግሎቶች

1. የሥራ ሂደቱ ተልዕኮ፤ ዓላማ ፤ራዕይ

ተልዕኮ/mission

በሴክተሩ ቀጣይነትና ዘላቂነት ያለውን ልማት ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት የበኩሉን ሚና ለመጫወት ያስቻለው ዘንድ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ፈጣን፤ጥራት ያለው፤ተደራሽና ዋጋው ተመጣጣኝ የሆነ የምርት ጥራትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ እንዲሁም የቴክኖሎጂ አመራረት እና የቴክኒክ ድጋፍና ምክር አገልግሎት አሰጣጥ ስልጠና መስጠት ነው'

7.2 ዓላማ/objectives

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራትና ምርታማነትን ሊያሳድጉ የሚችሉ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በማፈላለግ/በመፍጠር ሞዴል አምርቶ በማቅረብና እንዲጠቀሙበት በስልጠና በመደገፍ ኋላቀር ከሆነ አመራረት እንዲላቀቁ ማድረግ

7.3 ራዕይ/vision

በ2008 ዓ.ም. ጥ/አ/ኢንተርፕራዞች ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የምርት ጥራታቸውንና ምርታመነታቸውን አሳድገው በአገር አቀፍና በአለም አቀፍ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነው ማየት

2. የሚሰጠው ዋና ዋና አገልግሎት

2.1/ ቴክኖሎጂና የቴክኖሎጂ ዲዛይኖችን ከኢንተርኔት፣ከምርምር ተቋማት ከዩኒቨርስቲዎችና ከአካባቢው ህብረተሰብ በማፈላለግና በማሰባሰብ በሶፍት ኮፒና በሀርድ ኮፒ ማደራጀትና ሲፈለግ ለተጠቃሚው ማቅረብ

## 2.2 ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን ማምረት/ማቅረብ

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተቋማትና ለግል አምራች ድርጅቶ የሚያገለግሉ የተለያዩ ማሽነሪዎች ይመረታሉ

የተጠቃሚው ህብረተሰብ ሀሳብ መነሻ በማድረግ እና ገበያውን በማጥናት አዳዲስ ሞዴል ምርቶችን ቀጥሎ በተዘረዘሩት የሙያ መስኮች አምርቶ ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ማህበራት በማስተላለፍ ለገበያ እንዲያቀርቡ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

| | |
|---|---|
| የልብስ ስፌት ዉጤቶች | የብረታ ብረት ዉጤቶች |
| የቆዳ ዉጤቶች | የቀርከሃ ዉጤቶች |
| የማተምና ማቅለም ዉጤቶች | የሹራብ ዉጤቶች |
| የሽመና ዉጤቶች | የሸክላ ዉጤቶች |
| የእንጨት ዉጤቶች | የአግሮፕሮሰሲንግ ዉጤቶች |

2.3/ የቴክኖሎጂ አመራረት አጠቃቀምና የክህሎት ስልጠና መስጠት

| ተ.ቁ. | የስራው ዓይነት | የስልጠናው ዓይነት | የሚፈጀው ጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የልብስ ስፌትና ፓተርን አዘገጃጀት ስልጠና | መሠረታዊ ስልጠና | 3 ወር | |
| | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | ከ15ቀን - 1ወር | |
| | | የአመራረት ስልጠና | ከ1-9 ቀን | |
| 2 | የቆዳና ቆዳ ዉጤቶች ስልጠና<br>የማተምና ማቅለም ስልጠና<br>የሽመና ስራ ስልጠና | መሠረታዊ ስልጠና | 2ወር ከ15 ቀን | የሹራብ ስራ ስልጠና በመደራጀት ላይ ይገኛል |
| | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | ከ15ቀን-1ወር | |
| | | የአመራረት ስልጠና | ከ1-9ቀን | |
| 3 | የብረታ ብረት ስልጠና | መሠረታዊ ስልጠና | 4 ወር | |
| | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | ከ15ቀን-1ወር | |
| | | የአመራረት ስልጠና | ከ1-9ቀን | |
| 4 | የእንጨት ስልጠና | መሠረታዊ ስልጠና | 4 ወር | |
| | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | ከ15ቀን-1ወር | |
| | | የአመራረት ስልጠና | ከ1-9ቀን | |
| 5 | የቀርከሃ ስልጠና | መሠረታዊ ስልጠና | 2 ወር | |
| | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | ከ15ቀን-1ወር | |
| | | የአመራረት ስልጠና | ከ1-9ቀን | |
| 6 | የሸክላ ስራ ስልጠና | መሠረታዊ ስልጠና | 2 ወር | |
| | | የሙያ ማሻሻያ ስልጠና | ከ15ቀን-1ወር | |
| | | የአመራረት ስልጠና | ከ1-9ቀን | |
| 7 | የአግሮፕሮሰሲንግ ስልጠና | | | በመደራጀት ላይ ይገኛል |
| 8 | የኮንስትራክን ስልጠና | | | በመደራጀት ላይ ይገኛል |

2.4/ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና አመራረት የአሰልጣኞች ስልጠና መስጠት

ለቴክኒክና ሙያ መምህራን እና ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ልማት ኤጀንቶች የአሰልጣኞች ስልጠና በመስጠት በአካባቢያቸው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተቋማትን እንዲደግፉ ይደረጋል

2.5/ የምርት ማስተዋወቅ አገልግሎት መስጠት

የንግድ ባዛር በመሳተፍ ፣የንግድ ባዛር ኤግዚቢሽን ማዘጋጀት፣በማስሚዲያ ቅስቀሳ ማድረግ፣የምክክር (Forum) መድረክ በማመቻቸት፣መልካም ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስተላለፍ የቴክኖሎጂና ምርት በማስተዋወቅ ገበየ የማፈላለግ ስራ ይሰራል፡፡

2.6 ሙያዊ ድጋፍና የምክር አገልግሎት መስጠት

2.7 የምርት ሽያጭ ማከናወን

- የጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ምርቶች
- የእንጨትና ብረታ ብረት ምርቶች
- የቀርከሃ ምርቶች
- የአግሮ ፕሮሰሲንግ ምርቶች
- የኮንስትራክሽን ምርቶች

## አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚጠበቁ ቅድመ ሁኔታዎች

| ተ.ቁ | የሚሠጡ አገልግሎቶች | አገልግሎቱን የሚያገኙ አካሎች | ቅድመ ሁኔታዎች በየሙያ ዘርፉ |
|---|---|---|---|
| 1 | የአመራረት፣ አጠቃቀምና ክህሎት ክፍተት ስልጠና መስጠት | የጥቃቅንና አነስተኛ ድርጅቶች የግል ድርጅቶች<br>በቴክኒክና ሙያ ተቋማት ዉስጥ የሚያስተምሩ መምህራን<br>በኢንተርፕራይዞች ልማትና ድጋፍ አሰጣጥ ስር የሚገኙ የኢንዱስሪ ኤክስቴንሽን ልማት ኤጀንቶች | ለጥቃቅነና አነስተኛ ተቋማት በማህበር ተደራጅተው የሚሰሩ ስለመሆናቸው በአካባቢያቸው ከሚገኝ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማትና ድጋፍ አሰጣጥ ጽ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ስልጠናውን በነፃ ያገኛሉ<br>የግል ድርጅቶች ስልጠናውን ለመስጠት የሚያስፈልገውን የጥሬ ዕቃ ወጪ መሸፈን የሚጠበቅባቸው ሲሆን ክፍያውን በቅድሚያ ገቢ ያደርጋሉ |
| 2 | ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ | ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል | የጥሬ ዕቃ እና ኦቨርሄድ(የመብራት እና ማሽን) ወጪዎችን መክፈል ያስፈልጋል |
| 3 | የቴክኒክ ድጋፍና ምክር አገልግሎት ማድረግ | የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተቋማት | የድርጅቱን ማሽኖች ለሚጠቀሙ ደንበኞች ለማሽን አገልግሎት የሚሆን ዝቅተኛ ክፍያ የሚያስፈልግ ሲሆን አገልግሎቱን የሚያገኙት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ተቋማት ናቸው። |